http://www.freebirtukan.org
616.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

**Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia**

# <u>ብርቱካን ሚደቅሳ ላለፉት ስምንት ወራት እንደታመመች ተናገረች</u>

# <u>ለብርቱካን ሚደቅሳ ስንል ብቻ ሳይሆን ለራሳችን ስንል እንነሳ !</u>

መጋቢት 20 ቀን 2002

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በቃሊቲ እሥር ቤት በግፍና በጭካኔ እንድትማቅቅ ከተደረገ ይኸው 454 <u>አራት መቶ አምሳ አራት ቀናት</u> አልፈዋታል። ከነዚህ ቀናት ውስጥ ከአንድ መቶ ሰማኒያ ቀናት በላይ በጨላማ ቤት ውስጥ እንድትቀይ የተደረገ ሲሆን፣ ይሄም በማንም ነፍስ በገደለ ወንጀለኛ ላይ እንኳን ተደርጎ የማይታወቅ ትልቅ አሳዛኝና ኢሰብዓዊ ግፍ ነው።

በቅርቡ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እናት ወ/ሮ አልማዝ ገብረእግዚባሄር የልጃቸውን በጠና መታመም አሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ላይ ቀርበው ይፋ ካደረጉበት ጊዜ ጀመሮ፣ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ ሃዘናቸውንና ንዴታቸውን እየገለጹ ነው።

የ«ብርቱካን ትፈታ» ግብረ ኃይልም የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታመም እንዳሳሰበው የሚገልጽ፣ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ስልክ እንዲደወል ጥሪ ያስተላለፈ፣ የእንግሊዘኛ መግለጫ አውጥቷል። ይህ መግለጫ ተባዝቶ፣ የአሜሪካ የሕዝብ ምክር ቤት የአፍሪካ ጉዳይ ንኡስ ኮሚቴ ስብሰባ ባደረገበት ጊዜ በአዳራሹ ለነበሩ እንዲታደል የተደረገ ሲሆን፣ በዚያም የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በግፍ መታሰርና እያሽቆለቆለ የመጣው የጤንነቷ ሁኔታ ትልቅ አጀንዳ ሆኖ ነበር።

ምንም እንኳን የቃሊቲ እሥር ቤት ማረሚያ ቤት ሃላፊዎች፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን እንዲጎበኙ፣ ቅዳሜ መጋቢት 18 ቀን 2002 ዓ.ም ፣ በአዋሳ የሚኖረውን የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ወንድም፣ እሑድ መጋቢት 19 ቀን 2002 ዓ.ም ደግሞ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የክርስትና እናትን፣ ፍቃድ መስጠታቸው በአዎንታዊነት የሚታይ ቢሆንም፣ አሁንም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በከፍተኛ ሕመም ላይ እንዳለችና ሐኪም ሊያያት እንዳልቻለ ከቤተሰቦቿ በማረጋገጣችን እጅጉን በጣም አዝነናል።

http://www.freebirtukan.org
616.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ከመግባቷ በፊት ሙሉ ጤነኛ የነበረች እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን፣ ይህ በቅርብ ይፋ የሆነዉ ሕመሟ ወይዘሪቷ በጨለማ ቤት እንድትቀመጥ ተደርጋ የስነ ልቦና ቶርቸር በተፈጸመባት ጊዜ የጀመረ፣ ላለፉት ስምንት ወራት በተከታታይ ሲያሰቃያት የቆየ፣ እንቅልፍ እንዳትተኛ ያደረገ የጸና ሕመም እንደሆነ ወ/ት ብርቱካን ለቤተሰቦቿ ገልጻለች።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ለፍትህ፣ ለነጻነትና ለኢትዮጵያ አንድነት ስትል በግፍ የታሰረች አኩሪ እህታችን ናት። በሰዉ ሕይወት ላይ ያደረሰቻዉ አንዳች ጉዳት የለም። የጣሰችዉ አንድም የሕግ አንቀጽ የለም። በርሷ ላይ እየደረሰ ያለዉ ሕግን የማስከበር ሥራ ሳይሆን የበቀልና የጭካኔ ተግባር ነዉ።

በአዲስ አበባ የተቃዋሚ ድርጅቶች በሚያደርጉት ታላላቅ ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ በዉጭ አገር በተደረጉ አለም አቀፍ ሰላማዊ ሰልፎች፣ በተለያዩ ጊዜያት በተሰበሰቡ ፔትሽኖች፣ በየጋዜጣዉና በየድህረ ገጾች በሚወጡ መጣጥፎች እንደታየዉ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንድትፈታ ጥሪ አቅርበዋል። በርካታ የገዢዉ ፓርቲ ደጋፊዎችም ሁሉ ሳይቀር የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር ተገቢ እንዳልሆነ በመግልጽ የመፈታቷን አስፈላጊነት ገልጸዋል። እንደ ሴኔተር ራስ ፋይንጎልድ፣ ኮንግረስማን ዶናልድ ፔን፣ ወ/ሮ ጉኒላ ካርሰን የመሳሰሉ በርካታ የምእራባዉያን አገራት ባላሥልጣናት፣ እንዲሁም አምንስቲ ኢንተርናሽናልና ሂዉመን ራይት ዎችን ጨምሮ በርካታ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጓች ድርጅቶች በሙሉ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሕሊና እሥረኛ እንደሆነች ገልጸዉ፣ በአስቸኳይ መፈታት እንዳላበት ግፊት እያደረጉ ነዉ።

እንደዚያም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ ያሉ ባለሥልጣናት ከሁሉም ማእዘናት ለሚቀርቡላቸዉ ጥያቄዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዋል። እስከአሁን ድረስም ልባቸዉን እንደ ድንጋይ አደንድነዉ የጭካኔ ሥራቸዉን ቀጥለዉበታል።

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

**የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይ የቤተሰቧ ጉዳይ ብቻ አይደለም። በሊቀመንበርነት የምትመራዉ ድርጅቷ ጉዳይ ብቻ አይደለም። ለፍትህ ለሰላምና ለሰብዓዊነት የቆመ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ነው። የ«ብርቱካን ትፈታ» ግብረ ኃይል በመጠኑ አንዳንድ ሥራዎችን ለማስተባበር ቢንቀሳቀስም ዋናዉ ሥራ የሚሰራዉ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነዉ። በመሆኑም እያንዳንዱ ዜጋ የድርሻዉንና የሚችለዉን በትጋት እንዲያበረክት ጥሪ እናቀርባለን።**

**ይረዱ ዘንድ፣ ሊደረጉ የሚችሉ አንዳንድ ጠቃሚ፣ ሰላማዊና ሕጋዊ እንቅስቃሴዎችን እንደሚከተለዉ እናቀርባለን፡**

- **ፍትህ ሲዛባ ማየት የማይወድ የሰማይ አምላክ እግዚአብሄር በተአምራት እጁ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን እንዲፈዉሳት፣ የታሰረችበትን የወይኒ መዝጊያ እንዲሰብርና ከቤተሰቦቿና ከሁላችንም ጋር በአካል በሰላም እንዲያገናኛት ሁላችንም በተሰበረ መንፈስ፣ በንጹህ ልብና በትህትና ጸሎት ማቅረብ፤**

- **የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በማረሚያ ቤት የሚገኙ ታሳሪዎችን የመጠየቅ መብት ይሰጣል። በመሆኑም በአገር ቤት የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን፣ በቅርቡ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች እንዳደረጉት፣ ሊከለከሉ ቢችሉም፣ በቃሊቲ እሥር ቤት በየሳምንቱ እየሄዱ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ለመጠየቅ ሙከራ በማድረግ እሥር ቤቱን ማጨናነቅ፤**

- **የብርቱካን ሚደቅሳ ኬኔትራ በአደባባይ በመልበስና ፎቶግራፏንም በአደባባይ በመስቀል በግፍ ያሰሯት ግለሰቦች ብርቱካን ሚደቅሳን በሥጋ እንጂ በመንፈስ ማሰር እንደማይችሉ፣ በአካል ከኛ ቢለይዋትም ከልባችን ዉስጥ ግን ሊያወጧት እንደማይችሉ በማሳየት ማሳፈር፤**

- **በስደት የምንኖር ኢትዮጵያዉያን በዉጭ በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እየደወልን፣ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር ያለንን ተቃዉሞ በጨዋነት በመግልጽና በአስቸኳይ እንድትፈታ በመጠየቅ ኤምባሲዎችን በጥያቄዎቻችን ማጨናነቅ፤**

- **የአሜሪካ መንግስት የዉጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት፣ የአሜሪካን፣ የእንግሊዝና የሌሎች ኤምባሲዎችን በመደወል፣ በሚሊዮን በሚቆጠር ዶላር የሚደግፉት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ያሰረዉና እያሰቃየ ያለዉ መንግስት ላይ፣ ከቃላት ያለፈ ጫና እንዲያደርጉ በመጠይቅ፣ ስልካቸዉንና ኤሜሎቻቸዉን ማጨናነቅ፤ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ**

http://www.freebirtukan.org
616.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org



**በአስቸኳይ ህክምና እንድታገኝና እሷና ሌሎች የሕሊና እሰረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተፈተው በቅርቡ በሚደረገው ምርጫ እንዲካፈሉ ማድረግ**

**የመሳሰሉ ይገኙበታል።**

**ዝርዝር መረጃዎች፣ የስልክና የፋክስ ቁጥሮች፣ ኤሜል አድራሻዎችን ለማወቅ ወደ ሚከተለዉ የድህረ ገጽ አድራሻ እንዲሄዱ በአክብሮት እንጠይቃለን፡**

**http://www.freebirtukan.org**

**ዉድ ኢትዮጵያዉያን፡**

**ይህ የእያንዳንዳችን ሃላፊነት ነዉ። ይህ የእያንዳንዳች ጉዳይ ነዉ። እህታችን ለሕዝብ ነጻነት ስትል እየተሰቃየች፣ ዝም ማለት፣ ወይንም ሌሎች ብቻ እንዲንቀሳቀሱ መጠበቅ፣ ወይንም ሌሎችን ለምን አልሰሩም ብሎ መዉቀስ፣ ወይንም መናደድና ማዘን፣ ብቻዉን ለዉጥ አያመጣም። ከዚህ አልፈን መሄድ ይኖርብናል። «እኔ ምን አደረኩኝ?» ብለን ከራሳችን መጀመር አለብን።**

**ሕሊና ካለንና ካስተዋልን፣ በርግጥ ለወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና በግፍ ለታሰሩ የሕሊና እሥረኞች መፈታት የምናደገርገዉ እንቅስቃሴ፣ እራሳችንን ነጻ ለማወጣት የምናደርገዉ እንቅስቃሴ ነዉ። ለብርቱካን ሚደቅሳ ስንል ብቻ ሳይሆን ለራሳችን ስንል እንነሳ !**

**<u>በተጨማሪም፣ ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በእሥር ላይ እያለች፣ በጤንነቷ፣ በአካሏ፣ ወይንም በሕይወቷ ላይ፣ ያለሕግና ፍትሕ ጉዳት ቢደርስባት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የመንግስት ባለስልጣናትን በተጠያቂነት እንደሚይዝ አጥብቀን ልናስገነዝብ እንወዳለን።</u>**

**እግዚአብሄር ልባቸዉ ለደነደነ ማስተዋል ይስጣቸዉ !**

**በግፍ ለታሰረችዉ እህታችንም ጤናዋን ያብዛላት !**

**ለተቀረነዉ በዝምታችን ግፍን በተዘዋዋሪ መንገድ ከመደገፍ ይሰዉረን !**